# ሊነጋ ነው መሰል???

ከዓሣዬ

ጎሕ ሊፈነድቅ ነው ፤ ብሩህ ተሥፋን አዝሎ
ጽልመቱን ሊያጠፋው ጮራውን ፈንጥቆ
በገጠር ከተማ ዙሪያ ጥምጥም ከቦ ፤
አዎ !
የተዳፈነው ረመጥ እቶኑ እየጋለ
ሊነጋ ነው መሰል ?
የምሥራች በሉ ጸለምት ግዳይ ጣለ!

አለን አለን ያሉት የሆይ ሆይታ ባንዶች
የኩርኩም ሰለባ ፤ የጤዛ እርጋፊ ፤ የሙጃ ብቃዮች
የባዕዳን ድቅል ፤ የግንቦት አምካኞች
የግል ጥቅም አሣዳጅ ፤ የትግል አመንዝሮች
የአንጃ ልክፍቶች የዜሮ እባጮች
ጠባብ ብሔረተኛ ፤ የተገንጣይ ሃይሎች
ሳም ባልዋለችበት ኩበት ለቃሚዎች ፤
ለአንዲት ኢትዮጵያ ለሕዝቧ ስትሉ
በሉ አደብ ግዙ! ጎሕን ተከተሉ
በሁለ ገብ ዓመጽ ሊፋፋም ነው ትግሉ!

ነጋሪት ሲጎሰም ትግሉ ሲቀጣጠል
ለማይቀረው ሞቱ  በጥላው ሲደናበር
በሽብር ተንጦ የዘረኞች መንደር
እንዳበደ ውሻ ከወዲህ ወድያ ቢዘል
ጎሕ እንደሁ ጨክኗል ሊነጋ ነው መሰል፤
ግዳይ ሊጧጧፍ ነው ከተማም ባላገር
የምሥራች በሉ ልብ ይግዛ ከርስ አደር
ጠላትን በማውደም ከሃበሾች መንደር
ዳግም ትንሣኤዋን ለበላይ ለማብሰር
ሕዝቡን ተቀላቅሎ ታጥቋል የዓባዬ ዘር!

11/18/11